# የአንደኛየሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

## መግቢያ

### የተሰሎንቄ ከተማ

የተሰሎንቄ ከተማ በቴርማይክ የባህር ሰላጤ ራስጌ የምትገኝና ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያለባት የወደብ ከተማ ነበረች።ተሰሎንቄ የሮም ግዛት የሆነችው የመቄዶንያ ዋና እና ትልቋ ከተማ ነበረች። ከዚያም በላይ የታወቀች የመገናኛ እና የንግድ ማእከል ሆና ነበር።

### የተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን አመሰራረት

ጳውሎስ በሁለተኛው የመልእክተኛነት ጉዞው በሐዋ 16፡9 ላይ በራዕይ የመቄዶንያ ሰው ተሻገርና እርዳን ሲለው ተመልክቶ በመጀመርያ ወደፊሊጵስዩስ ከዚያም ወደ ተሰሎንቄ ከሲላስ ጋር ወንጌል ይዘው እንደገቡ በሓዋ 17፡ 1 ተጠቅሷል፤በዚህ ጊዜ ነበር ቤተክርስቲያኒቱ የተመሰረተችው። በተሰሎንቄ ይኖሩ የነበሩት አይሁድ የጳውሎስን አገልግሎት ተቃውመው ባስነሱት ሁከት ከከተማይቱ ሊወጡ ተገደዱ። በዚህ ምክንያት ተሰሎንቄን ለቀው ወደ ቤርያ ሄዱ ከተሰሎንቄ የወጡት አይሁድ እንደገና ባስነሱት ሁከት እነጳውሎስ ቤርያን ለቆ ወደ አቴንስ ለመሄድ ተገደዱ። ሐዋ 17፡ 10-15

### መቼ ና የት ተጻፈ

ከተማይቱን ለቀው ከወጡ ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መልዕክት ከቆሮንቶስ ከተማ ሆኖ ጻፈላቸው፣ ይህም በ50-52 ዓ/ም ውስጥ መሆኑ ይታመናል።

### የመልዕክቱ ዓላማ

ጳውሎስ በተሰሎንቄ ከተማ ለጥቂት ጊዜ ከቆየ በሁዋላ በድንገት ከተማዋን ለቆ ስለወጣ ሐዋ 17፡ 5-10 ከአህዛብ ወደጌታ የመጡትን አዳዲስ አማኞች በስደቱ ውስጥ የሚያጽናናቸው አልነበረም ጳውሎስ ይህን መልዕክት የጻፈበት ዓላማ በፈተና ውስጥ የነበሩትን አዳዲስ አማኞች ለማጽናናት ነበር 3፡3-5፤ የ'ሸውም ጳውሎስ መልእክቱን የጀመረው የተሰሎንቄ ምእመናን ስለነበራቸው ዕምነት በማመስገን ነው።1-10፤ ከዚያምበምእራፍ 2 ወንጌልን እርሱና አብረውት የነበሩት የወንጌል አገልጋዮች እንዴት በእነርሱ መሀል ያገለግሉ እንደነበርና ፤ የተሰሎንቄ ምእመናንም ወንጌሉን እንዴት እንደተቀበሉት በማስታወስ፣ ለእነርሱ ስላለው ፍቅር ይነግራቸዋል፣ ከዚያም በመቀጠል ማጽናናትና ምክርም ይሰጣቸዋል፤ በቅድስና እንዲኖሩ 4፡1-8፣ እርስ በርስ እንዲዋደዱ 4፡9-10 ፤እና ክርስቲያኖች እንደመሆናቸው መጠን መልካም ዜጎች መሆን እንዳለባቸው ያስገነዝባቸዋል፤ 4፡11-12።

### መሪ ሀሳብ

በመጨረሻም በ4፡13 እስከመጨረሻው በትንሳኤ ስላላቸው ተስፋ በመንገር የጌታን ምጽአት ነቅተው መጠበቅ እንዳለባቸው ያስገነዝባቸዋል። ደብዳቤው ለተለያ ዓላማ የተፃፈ ቢሆንም ሁለቱም የተሰሎንቄ መልዕክታት ይበልጥ የሚናገሩት ስለመጨረሻው ዘመን ነው ። ስለዚህ ይህ የመልዕክቱ መሪ ሐሳብ ተወስዶ ሊቆጠር ይችላል።

### የመወያያ ጥያቄዎች

ሐዋ 17፡1-5

1. እነጳውሎስ እንዴት ወደመቄዶንያ ሊሄዱ ቻሉ? ሐዋ 16፡9
2. ጳውሎስና ሲላስ ወደተሰሎንቄ ሲገቡ በመጀመርያ ያገለገሉት የት ነበር ለምን ይመስልሀል?
3. በተሰሎንቄ ለስንት ጊዜ አገለገሉ? ምንስ ነበር የስብከታቸው ማዕከል?
   ከቁጥር 5-9 ምን ተከናወነ?
4. ከዚያ ወዴት ሄዱ? የቤርያ ሰዎች ምን አይነት ሰዎች ነበሩ
5. በቁጥር 13-15 በተሰሎንቄ የነበሩት አይሁድ ምን አደረጉ?

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቁጥር 1

## 1ኛ የተሰሎንቄ መልእክት ምዕራፍ 1 ከቁጥር 1-10

## ምሳሌነት ያለው የህይወት ለውጥ

**መግቢያ**፡ ጳውሎስ ስለተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ምዕመናን የህይወት አስደናቂ ለውጥ በማንሳት እግዚአብሄርን ሲያመሰግን እንመለከታለን።

**ዓላማ**፡ ወንጌል ሰውን የመለወጥ ሀይል እንዳለው፤ በተጨማሪም የህይወት ለውጥ ከንግግር የበለጠ ወደውጪ የሚወጣ ምስክርነት እንዳለው ማሳየት።

**የንባብ ክፍል፥** የተሰሎንቄ መልእክት ምዕራፍ 1ከቁጥር 1-10

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ጳውሎስ በሰላምታው ውስጥ ያካተታቸው እነማን ናቸው ? ቁጥር1
2. ቁጥር 3 ጳውሎስ ስለተሰሎንቄ አማኞች ጌታን የሚያመሰግንባቸውን ምክንያቶች ምንድናቸው? በዝርዝር አስረዳ።
3. በቁጥር 4 ጳውሎስ የተሰሎንቄ አማኞች በእግዚአብሄር መመረጣቸውን እንዴት ያወቀ ይመስልሀል?
4. ወንጌል እንዴት ባለ ሁኔታ ነው ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች የመጣው? በዝርዝር ተናገረው። ቁጥር 5
5. የተሰሎንቄ ሰዎች ለማንና ፤ እንዴትስ ነው ምሳሌ የሆኑት? ምሳሌስ አድርገው የተከተሉት ማንን ነው? ቁጥር 6-7
6. ከተሰሎንቄ ሰዎች ህይወት ሁለት ነገሮች እንደወጡና በሌላ ስፍራ እንደተሰሙ ይናገራል? ምንድናቸው? ቁጥር 8
7. በቁጥር 9- 10 የህይወታቸው መለወጥን በተመለከተ ሰዎች ምን ነበር የሚናገሩት?

**ማዛመድ**፡
- በህይወትህ የዕምነት ስራ፤ የፍቅር ድካም ፤ የተስፋ ፅናት፤ እንደተሰሎንቄ ሰዎች ይታያል? ካልሆነስ ምን ልታደርግ ትወስናለህ?
- ህይወትህንና ቤተክርስቲያንህን ስትመለከት በውጪ ላሉት ሰዎች ምን ዓይነት ምስክርነት አለ ብለህ ትገምታለህ?

# <u>መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቁጥር 2</u>

## <u>1ኛ የተሰሎንቄ መልእክት ምዕራፍ 2 ከቁጥር 1-13</u>

## <u>ሞዴል የሆኑ አገልጋዮች።</u>

<u>መግቢያ፡</u> ጳውሎስና አብረውት ያሉት አገልጋዮች በእንዴት ባለ መሰጠትና ምሳሌ በመሆን ነቀፋ በሌለው ህይወት ጌታንና የተሰሎንቄን ሰዎች እንዳገለገሉ እንመለከታለን።

<u>ዓላማ</u>፡ አገልግሎታችን ራስን በመስጠትና፣ ነቀፋ በሌለበት፣ እንዲሁም ምሳሌነት ባለው መንገድ፣ ሊሆን እንደሚገባ መግለጽ።

<u>የንባብ ክፍል፡</u>1ኛ የተሰሎንቄ መልእክት ምዕራፍ 2 ከቁጥር 1-13።

<u>የመወያያ ጥያቄዎች፤</u>

1. እነጳውሎስ ወደተሰሎንቄ ከመምጣታቸው በፊት ምን ገጥሞአቸው ነበር? ወደዚያ አመጣጣቸውስ ምን ይመስል ነበር?
2. በቁጥር 3-6 እንዲህ አልተመላለስንም እያለ የሚዘረዝራቸው ፤ እውነተኛ አገልጋይ ሊጠነቀቅባቸው የሚገባው ባህርያት ምንድናቸው? ዘርዝራቸው።
3. በቁጥር 7 ያገለገሉበትን ፍቅር ከምን ጋር ያስተያዩታል? የእናት ፍቅር እንዴት ይገለጻል?
4. ቁጥር 8 ከወንጌል ሌላ ሊያካፍሏቸው ፈቃዳቸው የነበረው ነገር ምን ነበር? ለምን?
5. ከቁጥር 9-10 በምን ዓይነት ምሳሌነት በመካከላቸው ተመላለሱ?
6. በቁጥር 12 እንዴት እንዲራመዱ ነው የሚመክሯቸው? ራሳቸውን ከአባት ባህርይስ ጋር እንዴት ነው የሚያስተያዩት?
7. ቁጥር 13 የተሰሎንቄ ሰዎች በእንዴት ዓይነት መንገድ ቃሉን እንደተቀበሉ ይመሰክሩላቸዋል?

<u>ማዛመድ</u>፡

- በቁጥር 10 ጳውሎስ ...እናንተና እግዚአብሄር ምስክሮች ናችሁ። ይላል እንደዚህ ብለህ የምታገለግላቸውን ለመናገር ምን ያህል እውነተኛ ድፍረት አለህ? እንዲኖርህስ ምን ማድረግ ያለብህ ይመስልሀል?
- በአገልግሎትህ ነፍስህን እስከማካፈል እንዲሁም እንደእናት እና እንደአባት መሆን እንደሚያስፈልግህ ዛሬ ምን ያህል ተረዳህ?

# <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቁጥር 3</u>

## <u>1ኛ የተሰሎንቄ መልእክት ምዕራፍ 2 ፡ 14 እስከ ምእራፍ 3 1-13</u>

## <u>ሸክም ያለው አገልጋይ።</u>

<u>*መግቢያ፡*</u> *እነጳውሎስ በተሰሎንቄ አማኞች በደረሰው መከራ ምክንያት ሰይጣን እምነታቸውን እንዳያጠፋ ያላቸውን ሸክም ስጋትና ከዚህም የተነሳ ያሉበትን ለማወቅ ጢሞቴዎስን መላካቸውንና፣ ከዚያም በላይ ጸሎታቸውን እንመለከታለን።*

<u>**ዓላማ**</u>፡ ለምናገለግላቸው ሊኖረን ስለሚገባ የውስጥ ሸክም ና ፍቅር አስፈላጊነት  መማር።

<u>**የንባብ ክፍል፡**</u>
1ኛ የተሰሎንቄ መልእክት ምዕራፍ 2 ፡ 14 እስከ ምእራፍ 3 1-10

<u>**የመወያያ ጥያቄዎች**</u>

1. የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች በይሁዳ ያሉትን አማኞች የመሰሏቸው በምንድነው? ቁጥር 14-16 ክርስቲያኖች መከራ መቀበልን እንዴት ሊያዩት ይገባል?
2. ጳውሎስን ወደ ተሰሎንቄ እንዳይሄድ የከለከለው ማን ነበር? ቁጥር 18
3. ጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች እንዴት ነበር የሚቆጥራቸው? ቁጥር 19
4. ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ለምን ዓላማ ነበር ወደተሰሎንቄ የላከው? ቁጥር 1
5. ምን ነበር እምነታቸውን እንዳያናውጥ የፈራው? ቁጥር፡3። ለዚህ ደግሞ ተመርጠናል ሲልስ ምን ማለቱ እንደሆን ታስባለህ?
6. በቁጥር 5 ላይ ትልቁ ስጋቱ ምን ነበር?
7. ጢሞቴዎስ ከተሰሎንቄ ምን አይነት ዜና ይዞ ነው የተመለሰው? ይህስ በጳውሎስ ስሜት ላይ ምን ፈጠረ?
8. ቁጥር 8 ላይ ያለውን ሀሳብ አብራራው።
9. በቁጥር 9-13 ላይ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ያለው ሸክምና ጸሎት ምን ይመስል ነበር? በዝርዝር ተመልከተው ስለራሱስ ምን ይጸልያል?

<u>**ማዛመድ**</u>

- ጳውሎስ ለሚያገለግላቸው ያለው ሸክም፣ ስጋት በእና ጸሎት አንተን ምን አይነት አገልጋይ እንድትሆን ያስተምርሀል?
- ከሀዋርያቱ የጸሎት ህይወት ምን የምትማረው ነገር አለ

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቁጥር 4

## 1ኛ የተሰሎንቄ መልእክት ምዕራፍ 4 ፤ 1-12

## በተጠራንበት ጥሪ መመላለስ።

**መግቢያ፡** ቅዱስ የሆነው እግዚአብሄር ከርሱ ጋር ባለን ግንኙነት በቅድስና እንድንኖር ፣ እርስ በርሳችን ደግሞ በፍቅር፤ በውጪ ባሉት ፊት ዘንድ ደግሞ በአግባብ እንድንመላለስ ፈቃዱ እንደሆነ ያሳያቸዋል።

**ዓላማ**፡ በተጠራንበት በቅድስና፡ በፍቅርና፡ በአግባብ፡ መመላለስ እንደሚገባን ማሳየት።

**የንባብ ክፍል፡**
1ኛ የተሰሎንቄ መልእክት ምዕራፍ 4፡1-12

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ጳውሎስ የሚያደፋፍራቸው እና የሚያጽናናቸው ምን እንዲያደርጉ ነው? ቁጥር 1
2. ቅድስናን በተመለከተ የእግዚአብሄር ፈቃድ ምንድነው? በቁጥር 3 እና 7። ለነዚህ ክርስቲያኖችስ ለምን ይመስልሀል ስለዝሙት ማስጠንቀቂያ የሚሰጣቸው?
3. እያንዳንዱ የራሱን እቃ በቅድስናና በክብር መያዝ አለበት ሲል ምን ማለቱ ነው ብለህ ታስባለህ? ቁጥር 4
4. ስለምን ጉዳይ ነው ጌታ ይበቀላል የሚለው? ለምን? ቁጥር 6 ። 1 ቆሮ 6፡13-20
5. ወንድሙንስ አያታልል የሚለው ሀሳብ እንዴት ከዚህ ጋር ተያያዘ? ቁጥር 6
6. ይህን የጳውሎስን ማስጠንቀቂያ ቸል የሚል ማንን ይቃወማል ነው የሚለው? ቁጥር 8 ሐዋ5፡4
7. ለምንድነው ስለወንድማማች መዋደድ ማንም ሊጽፍላችሁ አይገባም የሚላቸው? ቁጥር 9
8. ሶስት ነገሮች በተለይ በውጪ ባሉቱ ዘንድ በአግባብ ስለመራመድ የሚጽፍላቸው ምንድነው? በዘመናችን ይህ ችግር ይታያል ወይ?

**ማዛመድ**

- ከዛሬው ጥናት ስለቅድስና ህይወት አስፈላጊነት አስተሳሰብረህን ያጠነከረልህ ምን ነገር አገኘህ?
- በውጪ ባሉቱ ዘንድ በአግባብ ስለመመላለስስ በዚህ ዘመን ላለን አማኞች ምን ምክርና ማስጠንቀቂያ አገኘህበት?

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቁጥር 5

## 1ኛ የተሰሎንቄ መልእክት ምዕራፍ 4፡13 - 5፡11

## ታላቁ ተስፋ

**መግቢያ**፡ ሐዋርያው የጌታን ምጽአት ነቅቶ ስለመጠበቅ የሰጠውን ማሳሰቢያ እንመለከታለን።

**ዓላማ**፡ የጌታ ምጽአት በማናስበው ሰአት እንደሆነ በመረዳት ሁልጊዜ ተዘጋጅተን ልንጠብቀው እንደሚገባ ለማስገንዘብ።

**የንባብ ክፍል፡** የተሰሎንቄ መልእክት ምዕራፍ 4፡13 - 5፡11

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በኢየሱስ ላንቀላፉት ወገኖቻቸው ምን የሚያጽናና ተስፋ ነው የሚሰጣቸው? ለምን እንቅልፍ አለው? ቁጥር 13
2. የትንሳኤያችን መሰረቱ በቁጥር 14 ላይ ምን መሆኑን ታያለህ? ጌታ ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋል ሲልስ ምን ማለቱ ነው?
3. ጌታ ሲመጣ ላንቀላፉትና ህያዋን ለሆንነው ምን ይከናወናል? ቁጥር 14-16
4. በቁጥር 16 ላይ የጌታ ምጽአት በምን አይነት ሁኔታ ይከናወናል?
5. መነሳት፣ መነጠቅ፣ ሁልጊዜ ከጌታ ጋር መኖር የሚሉትን ሀሳቦች ተነጋገሩባቸው? ቁጥር16-17
6. ቁ1 ጳውሎስ በድጋሚ ልንጽፍላችሁ አያስፈልግም የሚለው ሀሳብ ስለምንድነው? ለምን?
7. በቁጥር 3-4 ለማያምኑት ምጽአት ምን አይነት ሁኔታ ይፈጥርባቸዋል? ለኛስ ለምናምን?
8. በቁጥር 6-8 የብርሀን ልጆችና የጨለማ ልጆች ኑሮ ምን ይመስላል? እኛስ የ ምናምን ምን አይነት ኑሮ መኖር ይገባናል?
9. የምንነቃ ብንሆን ወይንም የምናንቀላፋ ብንሆን ሲል ምን ማለቱ ነው ቁጥር 10
10. ቁጥር 11 እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ አንዱም ሌላውን ያንጸው የሚለው ከላይ ካለው ሀሳብ ጋር እንዴት ይያያዛል?

ማዛመድ

- ስለምጽአት ማሰብ ምን ያህል ያጽናናል?4፤13  5፡11
- ጌታ ዛሬ ቢገለጥ ልትቀበለው ዝግጁ ነህ? በህይወትህ የሚታይህ ጉድለት ላስተካክለው ይገባኛል የምትለው ነገር አገኘህ ወይ?

# <u>መጽሀፍ ቅዱስ ጥናት ቁጥር 6</u>

## <u>የመጨረሻ ምክር</u>

<u>መግቢያ</u> የዛሬው ክፍል ምክር የሚያተኩረው ጌታ እስኪመለስ ከመሪዎቻችንና ከወገኖች እንዲሁም ከእግዚአብሄር ጋር ባለን ባለን ግንኙነት ምን አይነት ርምጃ እና አኗኗር ልንኖር  እንደሚገባን ማሳየት ነው።

<u>አላማ</u> ጌታ እስኪመለስ ሊኖረን የሚገባን የስነምግባር ኑሮ ምን ሊመስል እንደሚገባው ማስተማር።

<u>የንባብ ክፍል</u>
1 ተሰሎንቄ ምዕራፍ 5፡ከቁጥር12 እስከ 28

1. በቁጥር 12፣13 መሪዎችን እንዴት ብሎ ገልጸአቸዋል? ከነርሱ ጋርስ ምንስ አይነት ግንኙነት እንዲኖረን ይነግረናል?
2. በቁጥር 14 አንዳችን ለሌላችን ምን እንድናደርግ ይመክረናል?
3. በቁጥር 15 ለክፉ ልንመልሰው የሚገባን ምላሽ ምን መምሰል ይገባዋል?
4. ሁልጊዜና በሁሉ ሁኔታ የእግዚአብሄር ፈቃድ ለአማኞች ምን እንዲያደርጉ ነው?
5. በቁጥር19-22 የሰጣቸው ምክርና ማስጠንቀቂያ ምንድነው?
6. በጌታ መገለጥ ጊዜ አለነቀፋ እንዲጠበቅ የሚፈልገው ሁለንተናችንን ነው ። ሁለንተናችን ስንል ምን ማለት ነው?
   በዚህ ነገር የኛና የጌታ ድርሻ ምን ድነው?
7. በቁጥር 25-28 በምን አይነት ሁኔታ ክፍሉን ይደመድመዋል?

<u>ማዛመድ</u>:ከተዘረዘሩት ምክሮች በህይወት ጉዞህ የሚረዳህ ምን ነገር አገኘህ?